በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የሴቶች ክርስቲያናዊ ሕይወት


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ታህሳስ 18 ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የሴቶች ክርስቲያናዊ ሕይወት

- ስለ ሴቶች ስንናገር በዚህ ዓለም ያላቸውን አስፈላጊነት ባለመዘንጋት ሊሆን ይገባል፡፡
- ***በዘፍጥረት 1፡31*** ‹‹እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ፡፡›› ተብሎ የተጻፈው ውብ ቃል ነው፡፡
- ይሁን እንጂ በዚህ የሚያስደንቅ ሥነፍጥረት መካከል መልካም ያልሆነ ነገር ነበር፡፡ እርሱም ‹‹እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት፡፡›› ***ዘፍ 2፡18፡፡*** እንደተጻፈልን በሥነፍጥረት ያልተፈጸመ እግዚአብሔርም ሔዋንን በመፍጠር ፍጹም ያደረገው ይኽ ሥነ ፍጥረት ነበር፡፡
- በሔዋንም መፈጠር ዓለም መልካም ብቻ ሳይሆን እጅግ መልካም ሆናለች፡፡ ፍጥረትም በሔዋን መፈጠር ፍጹም ሆኖአል፡፡
- እግዚአብሔር ውሃን ለአትክልት አትክልቱንም ለሰውና ሕይወት ላላቸው ፍጥረታት የፈጠረው ሲሆን ሁሉን ለሰው አዘጋጅቶ በመጨረሻም ሔዋንን ፈጥሮአታል፡፡
- እግዚአብሔር አዳምን ከምድር አፈር ሔዋንንም አንዳችም ሕመም ለአዳም እንዳይሰማው አድርጎ ከሥጋና ከደም ፈጥሮአታል፡፡ በዚህም እግዚአብሔር ሕመም የሌለበትን ማደንዘዣ ያላስፈለገውን ሥራ ሠርቷል፡፡ ሕመምም የታወቀው አዳምና ሔዋን ከበደሉ በኋላ ነው፡፡
- ከሥነ ፍጥረት እንደምንረዳው ሔዋን በጾታ ከሔዋን ብትለይም በተፈጥሮ፣ በኃይል፣ በችሎታና በበረከት ግን ከአዳም እኩል ነበረች፡፡ ሁለቱም በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ተፈጥረዋልና፡፡

# የሴቶች ክርስቲያናዊ ሕይወት

- እግዚአብሔር ለሔዋን ከአዳም ጋር አድርጎ በምድር አራዊት፣ በሰማይ አዕዋፋት በባሕር ዓሦች ሁሉ ላይ እኩል ሥልጣን ሰጥቷታል፤ ‹‹ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ግዙአቸው፡፡›› *ዘፍጥ 1፡26-28፡፡*
- ሔዋን ይህንኑ ሥልጣን፣ በረከት፣ ተፈጥሮና በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ መፈጠርን ከአዳም እኩል ከእግዚአብሔር ተቀብላለች፡፡ አዳም ከአፈር ስለተገኘ አዳም ተብሎ ሲጠራ ሔዋን ግን ከአዳም ጎን ከአጥንቱና ከሥጋው ተገኝታለችና ሴት፣ የሰው ሁሉ ዘር እናት ስለሆነችም ሔዋን ተብላ ተጠርታለች፡፡
- የመጀመሪያ ስምዋ ተፈጥሮዋን ሁለተኛ ስምዋ እናትነትዋን የሚያመለክት ነው፡፡ አዳም አንድ ስም ሲኖረው ለእርስዋ ግን ሁለት ስም ነበራት፤ ከሰው (አዳም) ጋር እኩል ሁና ኖራለች፡፡
- በምንኖርበት ሕይወት ሴቶች ሁሉንም ሥራ መሥራት እንደሚችሉ እንረዳለን፡፡ ነገሥታትን ማግባት ሳያስፈልጋቸው ንግሥት ሆነዋል፡፡ አንዳንድ ሴቶችም የነገሥታቱን ዝናና ክብር የሚያስንቅ ሥራ በመሥራት ታላቅ ክብርን አግኝተዋል፡፡
- አስቴር ንጉሥን በማግባት ንግሥት ብትሆንም ዋናው ቁም ነገር ግን መላውን አገር ለመምራት የምትችልበት ችሎታ ይዛ መምራትዋ ነበር፡፡
- *በሐዋ 8፡27 እና ቀዳ ነገ 10፡1* የተጠቀሱት ኢትዮጵያውያን ንግሥታት በሥራቸው የነበሩትን ገዢዎች ሁሉ የሚመሩ ነበሩ፡፡

# የሴቶች ክርስቲያናዊ ሕይወት

- ሔዋን መልካም እንዳደረገች አድርጋ በማሰብ አዳምን ወደ ስህተት ብትመራውም ተጽዕኖ በማሳደር የመምራት ችሎታዋን ግን ተመልክተንበታል፡፡
- ታሪክ ወንዶቻቸውን በሚልቅ ኃይል፣ ችሎታና አቅም መምራት የቻሉ በርካታ ሴቶች ይነግረናል፡፡ ከእነዚህም የሚጠቀሱትን የዛሬ ሴቶች የመምራት ችሎታቸውን እንዳያጡ ስንል እናስታውሳቸዋለን፡-
  1. አቢግያ ዳዊትን ከበቀልና ከኃጢአት ተለይቶ መልካምን እንዲያደርግ ወደ መልካም ጎዳና መርታዋለች፡፡ ልበ አምላክ ዳዊትም ስለ ጥበብዋ ‹‹ወደ ደም እንዳልሄድ፥ በእጄም በቀል እንዳላደርግ ዛሬ የከለከለኝ አእምሮሽ የተመሰገነ ይሁን፥ አንቺም የተመሰገንሽ ሁኚ፡፡›› ***1ኛ ሳሙ 25፡33፡፡*** ይህች ሴት ልዩ የሆነውን - ነቢይ፣ የጦር አለቃና ንጉሥ መርታ ነበር፡፡
  2. ንግሥቲቱ ዲቦራ የጦር አለቃውንና ሕዝቡን መርታ ነበር፡፡ ***መሳ ምዕራፍ 4 እና 5፡፡***
  3. ከአሕዛብ ወገን በኢያሪኮ የነበረች ጋለሞታይቱ ረዓብ (ራኬብ) ሁለቱን የእስራኤል ሰላዮች በመምራት እግዚአብሔርን ወደ ማመን ቀርባለች፡፡ የጌታችን የትውልድ ሐረግ ውስጥ ገብታ በመቆጠርም መታሰቢያን አግኝታለች፡፡ ***ኢያ 2፤ ኢያ 6 እና ማቴ 1፡5፡፡***
  4. ቅድስት ሞኒካ ልጅዋን ቅ. አውግስጢኖስን ወደሚሻል መንፈሳዊ ደረጃ እንዲደርስ መርታው ነበር
- ሁሉንም የሴት መሪዎች ሕይወት አንስቶ ለመተረክ ጊዜ ያንሰናል፡፡ በዚህም ሴቶች የመምራት ችሎታና ማንነት እንደ ማያንሳቸው አረጋገጥን እንጂ የግድ ወንዶችን መምራት ይገባቸዋል እያልን አይደለንም፡፡

# የሴቶች ክርስቲያናዊ ሕይወት

- እንዲሁም ሴቶች የማይቻለውን መከራ ስለ ክርስቶስ ታግሰው ሰማዕታት እንደሆኑም እናውቃለን፡፡ ሴቶችም ከወንዶች ይልቅ መከራን የሚሸከሙ የሚችሉ ናቸው፡፡ የመምራት፣ የሁከተኛነት እና የሥልጣን ፍቅር ያለውን ወንድን መቻልዋና መታገስዋ ራሱ ለዚህ በቂ ማስረጃ ነው፡፡
- በርግጥም በሥልጣን ከሚደሰቱት ይልቅ በሥልጣን ታጋሽ ቻይ የሚሆኑ ብርቱዎች ናቸው፡፡
- ሴቶች የማገልገል መንፈስ የሌላቸውም አይደሉም፡፡
- በጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስለነበረው የሴቶች አገልግሎት ስንመለከት ሴቶች ዲያቆናይት፣ ደናግልና መበለቶች ሆነው ያገለግሉ እንደነበር እንረዳለን፡፡ እነዚህም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡
- ሴቶች ለቅድስና የሚያበቃ መልካም ሕይወት የሚጎድላቸው አይደሉም፡፡ ከእነዚህም ሴቶች መካከል የምትጠቀሰው ከሁሉም ሴቶች በላይ አማትዋን በመውደድ የተገኘችው ሩት ናት፡፡ በዚህም ትታሰብ ዘንድ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዘርዋ ተወልዷል፡፡ *ማቴ 1፡5፡፡*
- ሴቶች በጌታችን መዋዕለ ሥጋዌም የነበራቸው ድርሻም ይታወቃል፡፡ እንደ ጌታችን አምላካችን መድኃኒጻችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሴቶችን ያከበራቸው የለም፡፡
- በንጉሡ ቀኝ የምትቀመጥ ንግሥት የምንላት (*መዝ 44፡9*) የእመቤታችንን ሥጋ በመንሳት ሴቶችን ብሎም የሰውን ዘር ሁሉ አክብሮአል፡፡ በቤተ ክርስቲያናችንም ቅዳሴ ‹‹ማርያም ሆይ አንቺ ከኪሩቤልና ከሱራፌል ትበልጫለሽ፡፡›› እንላታለን፡፡ እንደ ሊቀ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልም በጸሎታችን እናነሳታለን፡፡ *ሉቃ 1፡26-38፡፡*

# የሴቶች ክርስቲያናዊ ሕይወት

- በጌታችን መዋዕለ ሥጋዌ በሕጻንነቱ ዘመን የነበሩ ሁሉንም የሴቶች ወገን የሚወክሉ ሦስት ሴቶች ነበሩ፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ደናግሉን፣ ቅድስት ኤልሳቤጥ ባለትዳሮችን፣ ሐናም መበለቶችን ይወክላሉ፡፡
- በመስቀሉም አጠገብ ሦስት ሴቶች (ማርያሞች) ነበሩ፡፡ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፣ እህትዋ የተባለች ማርያምና መግደላዊት ማርያም፡፡ *ዮሐ 19፡25፡፡*
- በጌታችን መዋዕለ ሥጋዌ የተከተሉትና ያገለገሉት ብዙ ሴቶች ነበሩ፡፡ *ሉቃ 8፡2-3፡፡*
- በበደል ለወደቁት ሴቶችም ከጌታችን ከአምላካችን በቀር የሚመለከታቸው የሚናገርላቸው አልነበራቸውም፡፡
- ‹‹እምነትሽ ታላቅ ነው፡፡›› *ማቴ 15፡28፡፡* በማለት ጌታችን እንዳደነቃት ሴት ያሉ ሴቶችም በጌታችን ክብር የተሰጣቸው ሴቶች ነበሩ፡፡
- ሽቱውን በእግሩ ላይ ስላፈሰሰችውም ሴት ጌታችን ‹‹ተዉአት፤ ስለ ምን ታደክሙአታላችሁ? መልካም ሥራ ሠርታልኛለች፡፡ ›› *ማር 14፡6፡፡* በማለት ተከራክሮላታል፡፡
- ሴቶች ይህንን ቃል ወስደው ለሚያስጨንቁአቸው ወንዶች መልስ አድርገው ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፡፡
- ሌላው ጌታችን ከመሰቀሉ አንድ ሳምንት አስቀድሞ በማርያምና በማርታ ቤት ያደረገው ነው፡፡ በዚህም ማርያም መማርን ትርጉሙን መረዳትን ማርታም አገልግሎትን የሚወክሉ ሆነው ተጠቅሰዋል፡፡ ይህም ምሳሌነት እስካሁን ድረስ ያገለግላል፡፡*ሉቃ 10፡38-42፡፡*

# የሴቶች ክርስቲያናዊ ሕይወት

- በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው ልዩ ገጽታ ያለውን ታሪክ እንመልከት፡፡ ይኸውም ጌታችን ከተወደደችው ከራሔል ሳይሆን ከተጠላችውና ካልተወደደችው ከልያ ዘር መወለዱ ነው፡፡
- የካህናትና የነገሥታት ነገድ የሆነው ይሁዳ የተገኘውም ከልያ ነው፡፡ እግዚአብሔርን ልያን በብዙ ልጆች ባርኮ ስለነበረ እህትዋ ራሔል ቀንታ ያዕቆብን ‹‹ልጅ ስጠኝ ይህስ ካልሆነ እሞታለሁ፡፡›› ***ዘፍጥ 30፡1*** ብላው ነበር፡፡ እግዚአብሔር በሰው ያልተወደደችውን ራሔልን ወዶአልና በዚህ ሐዘንም የተነሳ ራሔል እስከሞት ደርሳ ነበር፡፡
- እግዚአብሔር በምድር ላይ በፍትህ እጦች ወይም በኢፍትሐዊነት የተነሳ የተበደለች ሴት ካገኘ ክብሩን ሰጥቶ ከፍ ያደርጋት ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን የትኛዋም ሴት እንዳትበደል ጥንቃቄ የምታደርገውም ለዚሁ ነው፡፡
- ሴቶች ሌሎች መንፈሳዊ ፍሬዎች የማይገኙባቸው አይደሉም፡፡ ከሴቶችም መካከል በቤተ መቅደስ ባለ አምልኮ ምክንያት የምንጠቅሳት 84 ዓመት በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት ተወስና በመበለትነት የኖረች ነቢይቱ ሐና ለዚህ ነገር ምስክር ናት፡፡ ***ሉቃ 2፡36-38፡፡***
- በገዳማዊ ሕይወትም አልጋ ወራሾችን ወይም ነገሥታቱን ማግባትን እምቢኝ ብለው ሕይወታቸውን ለክርስቶስ የሰጡ ብዙ ሴቶች አሉ፡፡
- ሴቶች በጌታችን ስቅለትና ትንሣኤም ታማኝ አገልጋዮች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ***ዮሐ 20፡1-ፍም፡፡***

# <u>የሴቶች ክርስቲያናዊ ሕይወት</u>

- ሴቶች ፍቅራቸው ጸንቶ በመልካም ነገር ተነክተው በርትተው የሚገኙ መልካም የሆነውን የሰው ጠባይ የያዙ በምክንያቶችም ማስረዳት ከምንችለው በላይ መልካምነት የሚገኝባቸው ወንዶችን ወይም ባሎቻቸውን መግዛት የሚችሉ ናቸው፡፡
- እንደ ማርያም መግደላዊትና፣ ማርያም እንተ እፍረት ያሉ ብዙ ሴቶችም ከጥፋት ተመልሰው ከኃጢአተኝነት ተለይተው ለቅድስና በቅተዋል፡፡

***ቤተክርስቲያናችን ለእነዚህ ሴቶች ምን ታደርግላቸዋለች?***

- ቤተ ክርስቲያናችን ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር የተመረጠ መሥዋዕት አድርገው ያቀረቡ ሴቶችን ከመንበሩና ከቤተ መቅደሱ ውጪ ባለ አግልግሎት ይሳተፉ ዘንድ በዲያቆናይትነት ትሾማቸዋለች፡፡ ይህም በቤተ ክርስቲያን ትውፊትና በመጽሐፍ ቅዱስ የታወቀ አቅጣጫ ነው፡፡ <u>*የሐዋ 17፡4፣ ቀዳ ቆሮ 14፡34፣ ቲቶ 2፡3፡፡*</u>
- ቅዳሴያችን በጥንት የነበረ ዛሬም ያለ ነው፡፡ በውስጥ የቤተ መቅደስ አገልግሎቱ የሚሳተፉትም ቀድመው በብሉይ የተወሰኑ ዛሬም እንዲሁ እግዚአብሔር እንደፈቀደልን የሚቀጥሉ ናቸው፡፡
- በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ተቋማት ገብተው የሚማሩና የሚያስተምሩ ብዙ ሴቶች አሉ፡፡
- በቤተ ክርስቲያናችን ሰበካ በተለያዩ ክፍሎች፣ በሰንበት ት/ቤትም ተመድበው የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ሴቶች አሉ፡፡

# የሴቶች ክርስቲያናዊ ሕይወት

- ሴቶች መነኮሳይት በሚኖሩበት ገዳማት በምንኩስና የሚኖሩ፣ በየሆስፒታሉ የታመሙትን፣ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ቤተሰቦችን የሚጎበኙ በችግራቸው የተነሳ ከእግዚአብሔር እንዳይርቁ የሚያግዙ ብዙ ሴቶች አሉ፡፡ ሴቶች እነዚህን በመሰሉ መንገዶች እንዲያገለግሉም ቤተ ክርስቲያናችን ታበረታቸዋለች፡፡
- ከማጠቃለላችን በፊት ለሴቶች የሚከተሉትን ነገሮች ለማስታወስ እንወዳለን፡፡

1. የሚያስፈልጋችሁን በየደረጃው ለማግኘት የምትጣጣሩ ሁኑ እንጂ መጥፎ ውጤት ሊያስከትል በሚችል መልኩ የምትዘሏቸው ደረጃዎች አይኑሩ፡፡ ደረጃ በደረጃ እየወጣችሁ  በአንዱ ደረጃ የሚጠበቀውን ፈጽማችሁ ወደ ሚቀጥለው ማደግ በጀመራችሁት ለመቀጠል ይረዳልና መንፈሳዊ መንገዳችሁ እንዲህ ይሁን፡፡
2. መብታችሁን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውን ጥሬ ቃል በመያዝ የተረዳችሁት ከመሆን ይልቅ በአገልግሎትና በመንፈሳዊ ሕይወት በማደግ ራሳችሁን ተግባራዊ በሆነ መንፈሳዊ ሕይወት ፈትሹ፡፡
3. ፍላጎታችሁና ጥያቄአችሁ ተገቢ መነሻና መድረሻ ያለው ይሁን እንጂ በወንዶች ላይ ካላችሁ ንዴትና ቁጣ የመነጨ አይሁን፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን ወንዶች በመንፈሳዊ ሥልጣን የተሾሙ መሆናቸው በእግዚአብሔር የተፈቀደ ስለሆነ ይህን የሚለውጥ ምንም ዓይነት ዓለም አቀፋዊ አብዮት እንደማያስፈልግ ተረዱ፡፡ ወንዶችንም የሴትነት ጥበባችሁን፣ ብቃታችሁንና ችሎታችሁን ተጠቅማችሁ ተንከባከቡ፡፡

# የሴቶች ክርስቲያናዊ ሕይወት

4. ሁሉን ከእመቤታችን ተማሩ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በጌታችን ፊት ከፍ ያለ ክብር ያላት፣ ከደቀ መዛሙርቱ የላቀ መንፈሳዊ የሕይወት ደረጃ የነበራት ብትሆንም ቄስ ወይም ጳጳስ ልሁን የሚል ጥያቄ አላቀረበችም፤ ለሴቶች አልተፈቀደምና። እናንተም እመቤታችን ያልጠየቀችውን አትጠይቁ። የትኛዋም ሴት ምንም ያህል ታላቅ ብትሆን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ያላትን ደረጃ ልትመጥን አትችልምና ጊዜው ተለውጧል ሴቶችም አዳዲስ አመለካከቶችን እያዳበሩ ነው የሚል ሰበብ በሃይማኖት እንግዳ የሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌለውን አካሄድ አትፍጠሩ።
5. በዓለም ውስጥ ያሉ ልጆች የእናንተ ናቸውና በቤተ ክርስቲያን ባለ ተሳትፎአችሁና አገልግሎታችሁ ቤታችሁንና ቤተ ሰቦቻችሁን አትርሱ። የዓለማችንን ወንዶች በአግባቡ በማሳደግ ቤተ ክርስቲያንን በተዘዋዋሪ መንገድ ልትመሩ ትችላላችሁ፣ ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፥ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።›› *ምሳ 22፡6* እንዳለ ልጆችን ከልጅነታቸው ጀምሮ በማነጽ መልካም ሥራን በመሥራት አሳድጉ። ከሕይወት ጋር ያለን ግኑኝነት የተጀመረው በሴት እንደሆነ አንረሳም። ሰዎች ቀድመው የኖሩት በሴት (እናታቸው) ማኅፀን ነው፤ የጠቡትም የእናታቸውን ጡት ነውና - ይህንኑ እየመረመራችሁ በእግዚአብሔር የተፈቀደላችሁንና የተሰጣችሁን መንገድ ተከትላችሁ የምትራመዱና በሃይማኖት የምትኖሩ ሁኑ።

- ሴቶቻችን ሁሉ እግዚአብሔር በፈቀደላቸው መንገድ በመኖር ራሳቸውን እንዲጠቅሙ ለሌላውም ጥቅም እንዲሆኑ አምላካችን እግዚአብሔር በቸርነቱ ይርዳን፤ እመቤታችን በአማላጅነትዋ፣ ቅዱሳን መላእክትም በተራዳኢነት አትለዩን። አሜን!!!

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org